## ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

## ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ 14047

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡-- ዶ/ር ዳንኤል አለሙ

መልስ ሰጪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሮማነወርቅ የማነብርሃን

2. ወ/ሮ በቀለች ወረደ

3. ወ/ሮ ምስለአበባ ውቤ

*ውል - የግዴታ ዎች መቅረት - ሰለ ይርጋ - የውልን ጉዳይ ስለሚመለከት ማስረጃ- ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥሩ የህልና ግምቶች - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1856፣2024*

አመልካች ታህሳስ 1 ቀን 1981 ዓ.ም ከመ/ሰጭዎች ጋር ባደረጉት የጥብቅና ውል መሠረት ለሰጡት የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ብር 46000(አርባ ስድስት ሺ.ህ) እንዲከፈላቸው በ1988 ዓ.ም ያቀረቡትን ክስ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክሱ ክፍያው መጠየቅ ከነበረበት ጊዜ ሁለት ዓመት በኂላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2024(ለ) መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በሚል ውድቅ ስላደረውና ውሣኔውን ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስላጸና የቀረበ አቤቱታ፣

ውሣኔ፡- የሰበር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ጸንቷል፡፡

1. በፍብ/ሕ/ቁ 2024 በተደነገገው የሕግ ግምት ተጠቃሚ ያልሆነ ወገን (ከሣሽ) ክፍያው እንዳልተፈጸመ የማስረዳት ሸክም ያለበት ሲሆን ይኸን ሸክሙን መወጣት የሚችለው መሃላ በማውረድ ብቻ ነው፡፡
2. የሕሊና ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ደንብ ድንጋጌዎች የተለዩ ናቸው፡፡





ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፣- ዶ/ር ዳንኤል አለሙ

መልስ ሰሰጪዎች፡-1ኛ. ወ/ሮ ሮማነወርቅ የማነብርሃን በክርክሩ አልቀረቡም

2ኛ. ወ/ሮ በቀለች ወረደ }

3ኛ. ወ/ሮ ምስለአበባ ውቤ }

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

### ውሣኔ

አመልካች ለሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባፀናው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ የሰጠው አመልካች መልስ ሰጭዎች በፍርድ ቤት ያላቸውን የተለያዩ ጉዳዮች በተለየዩ መዝገቦች እነሱን ወክዬ እንድከራከር ወክለውኛል፣ የጥብቅና ውሉም ታህሳስ 1 ቀን 1981 ተፈርሟል፣ በውሉ መሠረት ለፈፀምኩት የጥብቅና አገልግሎት በአጠቃላይ ብር 46.000 (አርባ ስድስት ሺ.ህ) ይከፈለኝ በማለት ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ መልስ ሰጭዎች ለክሱ በሰጡት መልስ ውሉ የተፈፀመው በ1981 ሲሆን ክሱ ግን የቀረበው በ1988 ነው፣ ይሄውም የተጠቀሰውን ክፍያ ሳንጠየቅ ሁለት ዓመት ያለፈ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2024(ለ) መሠረት ክፍያው እንደተፈፀመ ይቆጠራል በማለት የተከራከሩ ሲሆን ሌሎች ክርክሮችንም አንስተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም መልስ ሰጭዎች ክፍያውን በጽሁፍ አላመኑም፣ ክሱ ከሁለት አመት ገደቡ በኂላ በመቅረቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024(ለ) መሠረት የህሊና ግምት እንዳይወሰድ መልስ ሰጭዎች የመሃላ ቃል እንዲሰጡ አልጠየቁም በመሆኑም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024(ለ) መሠረት ክፍያው መፈፀሙን የህሊና ግምት ወስዷል፡፡ በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይህንኑ ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ አጽንቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በተሰጠው ውሣኔ ላይ ሲሆን ይዘቱም ሲጠቃለል አመልካች የጥብቅና አገልግሎት የሰጠሁት በተለያዩ መዝገቦች ሲሆን የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄውም እንደየችሎቱ የክርክር ሂደት ጉዳዮች ተጠቃለው ውሣኔ ሲያገኙ መቅረብ የሚገባው በመሆኑ ጥያቄው በዚሁ መሠረት ቀርቧል፡፡ መልስ ሰጭዎች የጥብቅና ውሉ መፈፀሙን አልካዱም፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 ሊፈርስ የሚችል የህሊና ግምት የያዘ ነው፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2025 እና ተከታታዮቹ የሕሊና ግምቱ እንዳይወሰድ (ለማፍረስ) ያቀረብኩትን ክርክር ፍ/ቤቱ ሊመለከትልኝ ይገባ ነበር፣ ስለሆነም የሰበር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለፈፀመበት እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጭዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ የጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ባለመቅረባቸው ፍርድ ቤቱ በአመልካች በኩል የቀረበውን ማመልከቻ ብቻ መሠረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡፡

በቀረበው ጉዳይ በሰበር መታየት ያለበት ነጥብ የሥር ፍርድ ቤቶች በፍ.ብ.ሕ.ቁ 2024 የሰፈረውን የሕሊና ግምት አመልካች በመሠረተው ክስ ተፈፃሚ ያደረጉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ1981 ዓ.ም ከመልስ ሰጪዎች ጋር በመሰረትነው የጥብቅና ውል መነሻነት ሳበረከትኩት አገልግሎብ ብር 46.000 (አርባ ስድስት ሺ.ህ) ይከፈለኝ የሚል ነው፡፡ ከክሱ ይዘት ለመመልከት እንደሚቻለው አመልካች ከመልስ ሰሊዎች የሚፈልጉት ክፍያ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ነው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡት መልስ ሰጪዎች ከውሉ የሚመነጨውን የክፍያ ግዴታቸውን አልተወጡም በሚል ነው፡፡ የጥብቅና አበል መከፈል አለመከፈሉ አከራካሪ በሆነ ጊዜ የማስረዳት ሸክሙ የማን ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 (ለ) ከሁለት ዓመት በላይ የሆነውን የጥብቅና ክፍያ በሚመለከት የሕሊና ግምት በማስቀመጥ በውል የመክፈል ግዴታ ያለበት ወገን እንደከፈለ ይቆጠራል በማለት የሕግ ግምት ተጠቃሚ ያደርገዋል፡፡ በሌላ በኩልም በሕጉ 2026(1) ይህን የሕሊና ግምት ማፍረስ እንደማይቻልና የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ አልተከፈለኝም የሚል ወገን ያለው ብቸኛ ግምቱን የማፍረሻ አማራጭ መሃላ እንዲወርድለት መጠየቅ ብቻ መሆኑን ያስቀምጣል፡፡

በዚህ መሠረት መከፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ወይም ክፍያውን ያልጠየቀ ተዋዋይ በውሉ መሠረት የሚገባውን ክፍያ እንዳገኘ የሚገመትበት ብቻ ሳይሆን ክፍያው እንዳልተከፈለው የሚያስረዳው የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓትም ሌላ ፍሬ ነገርን ለማስረዳት ከሚከተለው ሥርዓት የተለየ ይሆናል፡፡ በመደበኛ የሙግት ሂደት የማስረዳት ሸክም ያለበት ወገን እንዲያስረዳ የሚጠበቅበትን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ብዙም የሕግ ገደብ የለበትም፡፡ ፍሬ ነገሩን ያስረዳልኛል የሚለውን ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ ይችላል፡፡ የጽሁፍ፣ የሰው ወይም የአካባቢ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ሸክሙን ሊወጣ ይችላል፡፡ በፍትሐብሄር ሕጉ 2024 የሚሸፈን ፍሬ ጉዳይ ባጋጠመ ጊዜ ግን የማስረዳት ሸክሙ ከአንዱ ወገን (ከተከሣሽ) ወደ ሌላው (ወደከሣሽ) ከመዛወሩ በተጨማሪ የማስረዳት ሸክሙን መወጣት የሚቻልበት የማስረጃ አይነትም ውሱን ነው፡፡ በ2026 መሠረት



የማስረዳት ሸክም የተሸጋገረበት ከሣሽ ይህን የማስረዳት ሸክሙን መወጣት የሚችለው መሃላ በማውረድ ብቻ ነው፡፡ ሌላ የትኛውም ዓይነት ማስረጃ ቢሆን የሕሊናውን ግምት ሊያፈርሰው አይችልም፡፡

በዚህ ህግ የሰፈረው የህሊና ግምት ከይርጋ ሕግ ጋር የሚያያዝ አይደለም፡፡ በ2024 የሰፈረው የሕሊና ግምት የማስረዳት ሸክም ከተከሣሽ ወደከሣሽ ያዞራል፣ የማስረዳት ሸክም የዞረበት ከሣሽ የሚያስረዳበትን መንገድ ይደነግጋል፡፡ በሆኑም በጊዜ ማለፍ ምክንያት ክሱ እንዲቋረጥ አያደርግም፡፡ የይርጋ ሕግ በሌላ በኩል በጊዜ ማለፍ ምክንያት የመከሰስ መብትን ስለሚያስቀር ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የማስረዳት ሸክም ያለበት ወገን ማነው? የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል አልተወጣም? ወዘተ- -ጥያቄዎችን በማንሣት ወደ ጉዳዩ ፍሬ ነገር ሊገባ አይችልም፡፡ በመሆኑም የይርጋው ጊዜ በፍ.ብ.ሕ ቁ.1845 መሠረት 10 ዓመት የሆነ ጉዳይ በዚሁ ሕግ 2024 በተደነገገው የሕሊና ግምት መሠረት ሊስተናገድ ይችላል፡፡ የይርጋ ጊዜው ያላለፈን ጉዳይ በሕጉ ቁጥር 2024 መሠረት እንደተከፈለ መቁጠር እርስ በርሱ የሚጋጭ ነገር ማከናወን አይደለም፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች ላቀረበው ክስ ምክንያት የሆነው ውል የተመሠረተው በ1981 ዓ.ም መሆኑን ግራ ቀኙ ተስማምተውበታል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሣሾች የሕጉ ግምት ተጠቃሚዎች ናቸው ያለው የተጠየቀው ክፍያ በ1981 ዓ.ም መከፈል የነበረበት ነው በማለት ነው፡፡ ለዚሁ መነሻ ያደረገው ተጨማሪ ፍሬ ነገር አመልካች ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ መከፈል ነበረበት በተባለው መጠን ላይ ወለድ መጠየቁ ነው፡፡ አመልካች በሌላ በኩል ክፍያው መከፈል የነበረበት ጊዜ ውሉ የተፈፀመበት 1981 ዓ.ም ሳይሆን ጉዳዩ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች የሚታይ በመሆኑ ውሣኔ የተሰጠበት ጊዜ መሆን ነበረበት ብሏል፡፡ ሆኖም ውሣኔ የተሰጠው መቼ እንደሆነ ለሰበር አቤቱታ ባቀረበው ማመልከቻ ላይ አልገለፀም፡፡ ሕጉ ከሚያዘው ከ2 ዓመት በታች መሆኑን ለማሣየት ክሱ ከቀረበበት ከ1988 ዓ.ም በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የተወሰነ መሆኑን ማስረዳት ሲኖርበት በዚህ ረገድ የቀረበ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም ውሉ የተፈረመበትና በከሣሽ መከፈል ከነበረበት ተብሎ ለወለድ ስሌት መሠረት የሆነውን 1981 ዓ.ም መነሻ መደረጉ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ክሱ በ1988 ዓ.ም የቀረበ እንደመሆኑ ተከሣሾቹ የፍ.ብ.ሕ.ቁ 2024(ለ) "ለጠቀቆች፣ ለውል አዋዋዮች ለሌሎችም የሕግ አማካሪዎች በሙያ ሥራቸው ወይም በሹመት ሥራቸው ላደረጉት

አገልግሎት የሚከፈል ዕዳ" ዕዳው መከፈል ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚለው የሕግ ግምት ተጠቃሚ ናቸው መባሉ በአግባቡ ነው፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሕግን ግምት ተፈጻሚ ከማድረግ አልፎ አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚል ውሣኔ ባለመስጠቱ እንደአመልካች አባባል በፍ.ብ.ሕ.ቁ 1845 የሰፈረውን የይርጋ ሕግ አለቦታው ተጠቅሞበታል ሊባል አይችልም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን ክስ በፍ.ብ.ሕ. 2024(ለ)ን መሠረት አድርጐ ውድቅ ማድረጉም ሆነ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 337 መሠረት ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስሀተት መፈፀሙን የሚያመለክት አይደለም፡፡
መልስ ሰጪዎች የሕግ ግምት ተጠቃሚ እስከሆኑ ድረስ፣ የውሉን መኖሩን አለመካዳቸው፣ በውሉ መሠረት ለመክፈል መስማማታቸውና ማመናቸው፣ ውሉ ፈርሷል ብለው አለመከራከራቸው ወዘተ… የሙግቱን ውጤት የሚቀይረው አይደለም፡፡ ውሉ አለ እንኳን ቢባል ዞሮ ዞሮ ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን እንደተከፈለ መቆጠሩ የሚቀር አይደለም፡፡ ይህ ሊቀር የሚችለው መሃላ እንዲወርድ ተጠይቆ እንደሆነና መሃላው የከሣሽን ክስ ያረጋገጠ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑ ከሰበር ማመልከቻውም ሆነ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገቡ የተገነዘብነው ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረበው የሰበር ማመልከቻ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

## ውሣኔ

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመቁ.5095 የካቲት 11 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡ ይጻፍ፡፡



## ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
## ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ 15835

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካቶች፡- ሼል ኢትዮጵያ አ/ማ
መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ

በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት የሙግት ተካፋይ ስለመሆን

- ስለ ባለ ጉደዩ ፍ/ቤት ሣይቀርብ መቅረት - የተከሣሽ ያለመቅረብ- ጉዳዩ ለመልስ በተቀጠረ ዕለት የተከሣሽ መልስ አለማቅረብ- የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥሮች 70፣233

የአሁኑ መልስ ሰጪ በከፍተኛው ፍ/ቤት በአመልካች ላይ በመሠረቱት ክስ የአሁን አመልካችን መልስ ለመቀበል በተያዘው ቀጠሮ ቀርቦ መልስ ባለማቅረቡ ፍ/ቤቱ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ መ/ሰጭ ክሱን በማሻሻላቸው የተሻሻለው ክስ እንደ አዲስ ክስ መቆር ስላለበት መልስ ልስጥበት በማለት አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውድቅ ስላደረገውና ይህንኑ ትእዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ስላጸናው የቀረበ አቤቱታ፣

<u>ው ሣ ኔ ፡-</u> የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጧቸው ትእዛዞች ተሽረዋል፡፡